የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ ሰኔ ፪ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No. 30
ADDIS ABABA, 9th June, 2026

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፲፪/፪ሺ፲፰

የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ……………………………………………………

………..……………………………………ገጽ ፲፱ሺ፯፻፫

## Content

Proclamation No. 1412/2026

The Ethiopian Aviation Security Proclamation (Amendment) Proclamation…………………

……………………….………...Page 19703

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፲፪/፪ሺ፲፰**

**<u>የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኪዩሪቲ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ</u>**

በአየር ትራንስፖርት ደህንነት፣ አስተማማኝነትና ቅልጥፍና ላይ እየጨመረ የመጣውን ተለዋዋጭ የደህንነት ስጋት በብቃት ለመከላከል የዓለም አቀፍ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ያወጣውን የተቀጽላ ፲፯ አስገዳጅ ስታንዳርዶችን ለማካተት፤ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ዘርፍ አቅም በቴክኖሎጂ ለማዘመን እና ተጨማሪ ሥልጣንና ተግባር መደንገግ በማስፈለጉ የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፪/፩ሺ፱፻፺፯ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

**PROCLAMATION No. 1412/2026**

**<u>A PROCLAMATION TO AMEND THE ETHIOPIAN AVIATION SECURITY PROCLAMATION</u>**

**WHEREAS,** it has become necessary to amend the Ethiopian Aviation Security Proclamation No. 432/2004 to incorporate International Civil Aviation Organization Annex 17 standards; to enhance the capacity of the aviation security sector with modern technology; and to provide additional powers and functions to counter the ever increasing threats of unlawful acts against the safety, regularity and efficiency of civil aviation;

**NOW THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፲፪/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. <u>ማሻሻያ</u>

የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፪/፩ሺ፱፻፺፯ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፦

፩/ "የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፬)፣ (፯)፣ እና (፲) ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬)፣ (፯)፣ እና (፲) ተተክተዋል፤"

"፬/ **"አደገኛ ቁሳቁስ"** ማለት በአውሮፕላኑ የመንገደኞች ክፍልም ሆነ በጭነት ማስቀመጫ ውስጥ ቢጫን የመንገደኞች ጤንነት፣ ደህንነት፣ ንብረት ወይም አካባቢ እንዲሁም የአውሮፕላኑን ደህንነት ስጋት ላይ የሚጥል ማንኛውም ዓይነት ቁሳቁስ ወይም ንጥረ ነገር ነው፤

፯/ **"ፍተሻ"** ማለት ሕገ ወጥ የጣልቃ ገብነት ለመፈጸም የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣ ፈንጂዎች ወይም ሌሎች አደገኛ ቁሳቁሶችን ቴክኒካዊ በሆነ ወይም በሌላ መንገድ ለይቶ ለማውጣትና ለማስቀረት የሚደረግ የሴኪዩሪቲ ቁጥጥር ነው፤

## 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as "The Ethiopian Aviation Security Proclamation (Amendment) Proclamation No. 1412/2026".

## 2. <u>Amendment</u>

The Ethiopian Aviation Security Proclamation No.432/2004 is hereby amended as follows:

1/ "Sub Articles (4), (7) and (10) of Article 2 are deleted and replaced by the following new Sub Articles (4), (7) and (10);"

"4/ **"Dangerous Goods"** shall mean any articles or substances which are capable of posing a risk to the health, safety, property or the environment of the passengers as well as the aircraft when transported either in the cabin or in the cargo compartment;

7/ **"Screening"** shall mean the application of technical or other means which are intended to identify or detect weapons, explosives or other dangerous devices, articles or substances which may be used to commit an act of unlawful interference;

፲/ **“ለደህንነት የተከለከሉ ስፍራዎች”** ማለት ለከፍተኛ ስጋት ተጋላጭ መሆናቸው የተለዩ በጥብቅ የተከለከሉ ወይም የሚጠበቁ እንዲሁም ተጨማሪ የደህንነት መቆጣጠሪያ ተግባራት የሚከናወንባቸው በኤርፖርት ውስጥ የሚገኙ ስፍራዎች ናቸው፤”

፪/ “አግባብነት ባላቸው ሕጎች በተደረገው የስያሜ ለውጥ መሰረት በአዋጁ ከተጠቀሱ ባለድርሻ አካላት የደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን የሚል ስያሜ ወደ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፤ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ኢንተርፕራይዝ ወደ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ስያሜ ለውጥ ተደርጓል፤”

፫/ “የአዋጁ አንቀጽ ፫ ርዕስ እና ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ ርዕስ እና ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፤”

**“፫. <u>የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት</u>**

፩/ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ በተቋቋመበት ሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የአቪዬሽን ሲኪዩሪቲ ስራዎችን በበላይነት ለማስፈጸም አግባብነት ያለው ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።”

10/ **“Security Restricted Area”** shall mean those areas of the airports which are identified as priority risk areas where in addition to access control, other security controls are applied;”

2/ “Without prejudice to the nomenclature given by other relevant laws, among the stakeholders mentioned in the Proclamation the Security, Immigration and Refugee Affairs Authority has changed to National Intelligence and Security Service; and the Ethiopian Airports and Ethiopian Airlines Enterprises has changed to the Ethiopian Airlines Group.”

3/ “The Title and Sub Article (1) of Article 3 of the Proclamation are hereby deleted and replaced with the following new Title and Sub Article (1);”

**“3. <u>National Intelligence and Security Service</u>**

1/ Without prejudice to the general responsibilities given to it under the law, the National Intelligence and Security Service Shall be the appropriate authority responsible for the overall implementation of this Proclamation.”

፬/ "ከአዋጁ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሀ) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ፊደል ተራ (ዘ)፣ (ገ)፣ (የ)፣ (ደ) እና (ጀ) ተጨምረዋል፤"

"ዘ) የአየር መንገድ ኦፕሬተሮች፣ የአየር ትራፊክ አገልግሎት ሰጪና የሌሎች ተቋማት የሴኪዩሪቲ ፕሮግራምና መመሪያ ከዚህ አዋጅ አንፃር ይገመግማል፤ ያጸድቃል፤

ገ) በአይሮፕላንና በአይሮፕላን ማረፊያ ጣቢያዎች ላይ ሕገ ወጥ ጣልቃ ገብነት ሊፈጸምባቸው የሚችሉ ከትከሻ የሚተኮስ የአየር መከላከያ መሳሪያ ወይም ስጋት ማድረስ የሚችል ማንኛውም ነገር ወይም ሰው አልባ አውሮፕላን ዝውውር ቁጥጥር ያደርጋል፤ ሊቃጣ የሚችል አደጋን ለመከላከል ስርዓት ይዘረጋል፤ እርምጃ ይወስዳል፤

የ) ወደ ኢትዮጵያ የሚበሩ ኦፕሬተሮች የበረራ ደህንነት ኦፊሰር ስምሪት ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል፤

ደ) ከዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ተቀጽላ ፲፯ እና ከሌሎች ሕጎች ጋር የተጣጣመ የተፃፈ ብሔራዊ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

4/ "The following new Paragraph (u), (v), (w), (x), and (y) are added after Sub Article (2) Paragraph (t) of Article 3 of the Proclamation;"

"u) evaluate; approve the conformity of airline operators and air traffic service providers security program and Directive in line with this Proclamation;

v) control the movement of Man-Portable Air-Defence Systems or anything cause threat to or unmanned aircraft that may use to unlawful interference; establish security measures to prevent potential threat and take action in the air craft and at the airport accordingly;

w) oversight inflight security officer deployment of operators fly to Ethiopia;

x) develop and implement a written national aviation security program compatible with Annex 17 of the International Civil Aviation Organization and other laws;

ጀ) ብሔራዊ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ጥራት ቁጥጥር የስራ ክፍል ያቋቁማል፤ ያለገደብ በማንኛውም ቦታ በመንቀሳቀስ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና መስፈርቶች አተገባበር ተገቢነት ያረጋግጣል፤ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤ ያስወስዳል፤"

፭/ "የአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ተሰርዟል፤"

፮/ "የአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል፤"

"፫/ የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኪዩሪቲ የስልጠና ፕሮግራም ይዘትንና የማሰልጠኛ ተቋማት የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ስለስልጠና ያወጣቸውን ደረጃዎችና ተመራጭ ሀሳቦችን የጠበቁ ስለመሆናቸው ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ጋር በጋራ ያረጋግጣል።"

፯/ "ከአዋጁ አንቀጽ ፯ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጾች ፰፣ ፱፣ ፲፣ እና ፲፩ ተጨምረዉ ከአንቀጽ ፰ እስከ ፳፩ የተቀመጡ ነባር ድንጋጌዎች እንደቅደም ተከተላቸዉ ከአንቀጽ ፲፪ እስከ ፳፭ ሆነዉ ተሸጋሽገዋል፤"

"፰. **የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር**

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፦

y) establish a National Aviation Security Quality Control work unit; ensure the appropriate implementation of aviation security policies, programs and standards with unlimited access; take corrective action; "

5/ "Sub Article (1) and (2) of Article 4 of the Proclamation are hereby deleted;"

6/ "Sub Article (3) of Article 4 of the Proclamation is hereby deleted and replaced with the following new Sub Article (3);"

"3) Ensure the content of the Ethiopian aviation security training program and training institution meet the standards and recommended Practice of the international civil aviation organization in collaboration with the national intelligence and security Service."

7/ "The following new Articles 8, 9, 10 and 11 are added after Article 7 of the Proclamation and the existing Articles 8 to 21 are renumbered as Article 12 to 25 respectively;"

"8. **Information Network Security Administration**

Without prejudice to the power given to it under the law, the Information Network Security Administration:

፩/ በአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ አካላት የሳይበር ደህንነት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ድጋፍ ያደርጋል፤

፪/ በአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨባጭ የሆነ የሳይበር ደህንነት ስጋት መኖሩ ሲረጋገጥ የጥንቃቄ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤

፫/ በየኤርፖርቶች ደረጃ በሚቋቋሙት የሴኪዩሪቲ ኮሚቴዎች ውስጥ በአባልነት ይሳተፋል ።

1/ Support for entities employed in the aviation industry to execute their responsibility in maintaining cyber security;

2/ Provide early warning when a confirmed substantial cyber security threat exists against the aviation industry;

3/ Participates as a member in all security committees to be established at airport level.

፱. <u>**የኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት**</u>

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት፦

፩/ የአቪዬሽን ደህንነት ለመጠበቅ ስራ ላይ የሚውሉ የአርቴፊሻ ኢንተለጀንስ ቴክኖሎጂዎችን በማዘመን ረገድ ድጋፍ ያደርጋል፤

፪/ የአቪዬሽን ደህንነት ተግባራት በጥራት፣ በቅልጥፍናና በብቃት እንዲፈፀሙ ድጋፍ ያደርጋል፤

፫/ በኤርፖርቶች ደረጃ በሚቋቋሙት የሴኪዩሪቲ ኮሚቴዎች ውስጥ በአባልነት ይሳተፋል ።

9. <u>**Ethiopian Artificial Intelligence Institute**</u>

Without prejudice to the responsibilities vested to it by law, the Ethiopian Artificial Intelligence Institute:

1/ Provide support to advance Artificial Intelligence technologies used to maintain the safety of the aviation industry;

2/ Provide support to execute the aviation security activities with quality, efficiently and effectively;

3/ Participates as a member in all security committees to be established at airport level.

**፲. <u>የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት</u>**

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት፡-

፩/ የኢሚግሬሽን ቁጥጥር የሚከናወንባቸውን የኤርፖርት ኢሚግሬሽን ኬላዎችና ስፍራዎች ይቆጣጠራል፤

፪/ በሕግ ማዕቀፍ በተዘረጋው የአሠራር ሥርዓት መሰረት የመንገደኞች ምዝገባ እና ቅድመ በረራ መረጃን ይሰበስባል፤ የተሰበሰበውን መረጃ ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ተደራሽ ያደርጋል፤

፫/ ለኤርፖርቱና ለአየር ትራንስፖርት ሥርዓት ደህንነት ስጋት በሆኑ ጉዳዮች ላይ መረጃ ይለዋወጣል፤

፬/ በኤርፖርቶች ደረጃ በሚቋቋሙት የሴኪዩሪቲ ኮሚቴዎች ውስጥ በአባልነት ይሳተፋል።

**፲፩. <u>የጉምሩክ ኮሚሽን</u>**

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የጉምሩክ ኮሚሽን፡-

፩/ የጉምሩክ ቁጥጥር የሚከናወንባቸው የኤርፖርት ጉምሩክ ስፍራዎችን ይቆጣጠራል፤

**10. <u>Immigration and Citizenship Service</u>**

Without prejudice to the responsibilities vested to it by law, the Immigration and Citizenship Service;

1/ Controls airport immigration checking points and working areas;

2/ Collects Passenger Registration and Advance Passenger Information in accordance with the operating procedures established within the legal framework; makes the collected information accessible to the National Intelligence and Security Service;

3/ Exchanges information on issues threats to the airport and air transport system;

4/ Participates as a member in all security committees to be established at airport level.

**11. <u>Custom Commission</u>**

Without prejudice to the responsibilities vested to it by law, the Custom Commission shall have the following duties and responsibilities:

1/ Control airport custom working areas;

፪/ ለኤርፖርቱና ለአየር ትራንስፖርት ስርዓት ደህንነት ስጋት በሆኑ ጉዳዮች ላይ መረጃ ይለዋወጣል፤

፫/ በኤርፖርቶች ደረጃ በሚቋቋሙት የሴኪዩሪቲ ኮሚቴዎች ውስጥ በአባልነት ይሳተፋል።”

፰/ “ከአዋጁ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሰ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፯) እንደተሸጋሸገ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ፊደል ተራ (ሸ)፣ (ቀ)፣ (በ) እና (ተ) ተጨምረዋል፤”

(ሸ) የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር --------------------------------------------አባል፤

(ቀ) የኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት-----------------------------አባል፤

(በ) የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት--------- --------------------------------------------አባል፤

(ተ) የጉምሩክ ኮሚሽን------------------------------- --------------------------------------------አባል።”

፱/ “ከአዋጁ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፯) እንደተሸጋሸገ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል፤”

“፫/ በኢትዮጵያ በኩል የሚጓዙ ተላላፊ መንገደኞች በተቀጽላ ፲፯ የተቀመጠውን የሴኪዩሪቲ መስፈርት ያሟሉ ሆኖ ሲገኝ በሀገር ወስጥ ከሚደረግላቸው የመንገደኞች እና የጉዞ እቃዎቻቸው ፍተሻ ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ።”

2/ Exchange information on issues threats to the airport and air transport system;

3/ Participates as a member in all security committees to be established at airport level.”

8/ **“**The following new Paragraph (i), (j), (k), and (l) are added after Sub Article (2) Paragraph (g) of Article 9 of the Proclamation as renumbered by Sub Article (7) of Article 2 of this Proclamation;**”**

“i) Information Network Security Administration-------------Member;

j) Ethiopian Artificial Intelligence Institute---------------------Member;

k) Immigration and Citizenship Service----------------------Member;

l) Custom Commission------------------ ------------------------------Member.”

9/ “The following new Sub Article (3) is added after Sub Article (2) of Article 13 of the Proclamation as renumbered by Sub Article (7) of Article 2 of this Proclamation;”

“3/ Transfer passengers and their baggage traveling via Ethiopia may be exempted from security screening provided they meet the security requirements set forth in Annex 17.”

፲/ “ከአዋጁ አንቀጽ ፲፯ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፯) እንደተሸጋሸገ በሚከተለው አዲስ ርዕስ እና ንዑስ አንቀጾች ተተክተዋል ከአንቀጽ ፲፰ እስከ ፳፩ የተቀመጡ ነባር ድንጋጌዎች እንደቅደም ተከተላቸዉ ከአንቀጽ ፲፰ እስከ ፳፭ ሆነዉ ተሸጋሽገዋል፤”

“፲፯. **<u>ስለ አቪዬሽን ሴኪዩሪቲ አገልግሎት ክፍያ አከፋፈልና ወጪ አሸፋፈን</u>**

፩/ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ተመራጭ ሃሳቦችን ተከትሎ ከራሱ መንገደኞች፣ ከሌሎች ኦፕሬተሮች እና በኤርፖርት ውስጥ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ አገልግሎት ከሚያገኙ ማናቸውም አካላት የአገልግሎት ክፍያ በመሰብሰብ ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ገቢ ያደርጋል። ይህም በሁለቱ ተቋማት የጋራ ስምምነት የሚፈጸም ይሆናል።

10/ “The following Article 17 as renumbered by Sub Article (7) of Article 2 of this Proclamation are replaced with the following new Title and Sub Articles and the existing Article 18 to 21 are renumbered as Article 18 to 25 of the Proclamation respectively;”

“**17. <u>Aviation Security Service Charges and Cost Recovery</u>**

1/ Ethiopian Airlines Group shall, in accordance with the International Civil Aviation Organizations recommended practices, collect the aviation security service fee from its own passengers, other operators and any entities that receive aviation security services at the airport; and remit it to the National Intelligence and Security Service. The execution of this arrangement shall be governed by mutual agreement between the two institutions.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸውን የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ አገልግሎት የክፍያ ተመን የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ተመራጭ ሃሳቦችን ተከትሎ በየጊዜው እየተጠና በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እና በኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ በጋራ ይወስናሉ፤ ያሻሽላሉ።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከተውን የክፍያ ተመን የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ባለው ተቋማዊ አሠራር መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከተው የአገልግሎት ክፍያ ከመንገደኞች እና ጭነት አጓጓዦች ላይ ወጪን የመተካት መርህ ተከትሎ የሚሰበሰብ ይሆናል።

2/ The security fee tariff stated under sub article (1) of this Article shall be periodically reviewed and jointly decided by the National intelligence and security service and Ethiopian airline group in accordance with the International Civil Aviation Organization recommended practices.

3/ The Ethiopian Civil Aviation Authority shall notify the fee tariff referred to in sub Articles (1) and (2) of this Article to the concerned bodies in accordance with its institutional procedures.

4/ The service fee referred to in sub Articles (1) and (2) of this article shall be collected from passengers and cargo carriers in accordance with the cost recovery principle.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፬) የተመለከተው የአገልግሎት ክፍያ ለኤርፖርት የሴኪዩሪቲ ቴክኖሎጂ ግዢ፣ ለአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ የጸጥታ አካላት ሥልጠናና አቅም ግንባታ፣ (የአቪዬሽን ፖሊስን ጨምሮ) ለአነፍናፊ ውሻ ግዥና ሥልጠና፣ ለጥገናና ማስፋፊያ እንዲሁም አሠራርን ለማዘመን የሚውል ሲሆን መደበኛ ደመወዝ እና ሥራ ማስኬጃን አይጨምርም።

፮/ አዲስ ለሚገነቡ ኤርፖርቶች የሚውል የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ፋሲሊቲ ግንባታዎች፣ ቴክኖሎጂ ግዢዎች እና ተያያዥ ወጪዎች በኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ይሸፈናል።"

**፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፪ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀ ሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

5/ The service fee stated under Sub Articles (1), (2) and (4) of this Article, except for the salaries and operational expenses, shall bear the expenditure of airport security technology procurement; training and capacity building of aviation security personnel (including aviation police); procurement and training of K9 dogs; maintenance and expansion; and updating of operations.

6/ The expenditure to aviation security facility construction, technology procurement and related costs subject to newly constructed airport shall bear by the Ethiopian airline group."

**3. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force upon the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 9th Day of June, 2026**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**